4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቀን ግንቦት ፳ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.
ቁ. 20/09

# በስደት ላይ ያለው ህጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፳፯ኛ መደበኛ ጉባኤ መግለጫ

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ላይ ያለው ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ፳፯ኛ መደበኛ ጉባኤውን በሴይንት ፖል ሚኒሶታ በሚገኘው በደብረ ብርሃን ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን አካሂዶአል። ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያናችን ያለችበትን ሁኔታ፥ የጊዜውንም አሳሳቢ ጥያቄዎች በጥልቀት ተወያይቶአል። ጉባኤውም ቤተ ክርስቲያን የምትስፋፋበትን፥ ህገ ቤተ ክርስቲያን እንዲከበር፥ ህዝበ ክርስቲያንም ከስህተትና ከግራ መጋባት የሚጠበቁበትን በተለይም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ያሉ ኦርቶዶክሳውያን በጽንዓት ሃይማኖታቸውን የሚጠብቁበትን የሚከተሉትን ውሳኔዎችና መግለጫዎች አውጥቶአል።

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ባሳለፈችው የሁለት ሺ ዓመት ታሪኳ ውስጥ ለልጆቹዋ የመንፈሳዊውም ሆነ የሥጋዊው ዕውቀት ምንጭ በመሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ተጠብቃና በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ ወደ እኛ ደርሳለች፤ ይህም ሲሆን ጉዞዋ ብዙ ውጣ ውረዶችን በታላቅ ተጋድሎ በማለፍ ነው። የዮዲት ጉዲት ቁጣ፥ የኦቶማን ቱርክና የግራኝ አህመድ ሰይፍ፥ የነበርሙዴዝ ተንኮል፥የፋሽሽት ጣልያን መርዝ ቤተ ክርስቲያኒቷን ያልፈታት ልጆቹዋ በአንድ ልብ ሆነው በፍቅር በአንድነት ስለቆሙ ነው። አሁንም በእኛ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን በየአቅጣጫው እየተወረወረባትም ያለውን ፈተና ማለፍ የምትችለው አንድ ልብ ሆነን ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን ስንቆም ነው። ስለሆነም በአገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም በስደት ያላችሁ ካህናትና ምእመናን ህገ ቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በማክበር በፍቅር በአንድነት ቤተ ክርስቲያናችሁን እንድተጠብቁ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለሰላም የቆመች፥ፍቅርንና አንድነትን በህዝቦቹዋ ዘንድ ስትሰብክ የኖረች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፤ በአገራችን በኢትዮጵያም ለዘመናት ተጠብቆ የቆየው የሃይማኖት መቻቻልና መከባበር እንዲሁ በባዶ የተገኘ ሳይሆን፥ የዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተግባር ያፈራው ነው። ሆኖም ግን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአገራችን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የሃይማኖት አለመቻቻል፥ የአብያተ ክርስቲያናት መደፈርና ከየቦታው የሚሰማው ኃይለ ቃል ቅዱስ ሲኖዶስን እያሳዘነው ነው። በመሆኑም አገራችን ያላትን ታላቅ የሆነ አብሮ የመኖር ታሪክ የምታውቁ የአገር ሽማግሌዎች ፥ የሃይማኖት ፥ የፖለቲካና ሆነ የሰብአዊ መብት መሪዎች፥ ህዝብ ከህዝብ ጋር የሚቀራረብበትን መንገድ እንዲፈልጉ በማሳሰብ ፥ አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎችም የሃይማኖትን ነገር የፖለቲካ ትርጉም በመስጠት በችኮላ በአደባባይ የሚሰጡት መግለጫ አብሮ የኖረን ህዝብ ይባስ የሚያራርቅ ልብ የሚያሻክር ስለሚሆን ከዚህ እንዲታቀቡ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

3. በስደት ያለው ቅዱስ ሲኖዶስ ሐዋርያዊ ተልእኮውን በሰሜን አሜሪካ በአውሮፓ በአፍሪካ፥ በአውስትራሊያና በኒውዚላንድ አህጉራት እየተወጣ ይገኛል፤ ቅዱስ ሲኖዶሱ ተልእኮውን በበለጠ ተግባራዊ እንዲያደርግ ግን አብያተ ክርስቲያናት በሲኖዶሱ ውስጠ ደንብ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መመራት ይኖርባቸዋል፤ በመሆኑም በህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ፥ ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ያወጣውን የቃለ አዋዲ ውስጠ ደንብ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ያሳስባል።

4. ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ፥ በስደት በመላው ዓለም የተበተነውን ሕዝብ በትምህርተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮው ሲያጽናና ሲመክር የኖረ ነው። በዚህም መሠረት በቅርቡ በብፁዕ አቡነ ኤልያስ የአውሮፓና የአፍሪካ ሊቀ ጳጳስና በሰባኬ ወንጌል አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ በደቡብ አፍሪካና በአካባቢው ባሉ አገሮች እንዲሁም በኡጋንዳ የተደረገውን አገልግሎት ሪፖርት በታላቅ አድናቆት አድምጦአል። በስደት ያለውም ህዝባችን በመከራውና በችግሩ ሳይቀር ስለሃይማኖቱ የሚያሳየውን ጽንአት ቅዱስ ሲኖዶስ በምስጋና ተመልክቶአል፤ በዚህም ብፁዕ አቡነ ኤልያስ አባታዊና ሐዋርያዊ ተግባራቸውን ለመወጣት እያደረጉ ያሉትን ጥረት፥ እንዲሁም ኦርቶዶክሳዊው ሰባኬ ወንጌል አባ ወልደ ትንሣኤም በአፍሪካ አገሮች ከሰጡት አስደናቂ የሰብከተ ወንጌል አገልግሎት በተጨማሪ፥ በአሁኑ ወቅት በአውስትራልያ እያከናወኑ ያሉትን ሐዋርያዊ ተልእኮ ቤተ ክርስቲያን በማድነቅ ምስጋና አቅርቦአል። እንዲሁም በብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የአሪዞናና የኔቫዳ አህጉረ ስብከቶች ሊቀ ጳጳስ አማካይነት፥ በአውሮፓ በጀርመን የተከናወነውንም ሐዋርያዊ ተልእኮ ሪፖርት ጉባኤው አድምጦአል። በጀርመንም በአውስትራልያም ያሉ የቤተክርስቲያኒቱን ልጆች አበው ካህናትና ህዝበ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በመፍራት፥ የሃገራቸውንና የቤተ ክርስቲያናቸውን ታሪክና ሃይማኖት ለልጆቻቸው ለማስተላለፍ የሚያደርጉትን ጥረት በጥሞና በመመልከት ጉባኤው የማበረታቻ መልእክቱን አስተላልፎአል።

5. በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም ያሉን ቅዱሳት መካናት፥ የረጅም ጊዜ የሃይማኖትና የአገር ታሪክ ምስክሮች ናቸው። እነዚህ ቦታዎች ተጠብቀው የቆዩትም እንደዛሬው ዘመናዊ መጓጓዣ ሳይኖር አባቶቻችንና እናቶቻችን ረጅም ጉዞ በ በግብጽና በቀይ ባህር በረሃዎች በማድረግ ፥ ገሚሶቹ ከረሃብና ከጥም የተነሳ በየበረሃው ወድቀው እየቀሩ በበሽታ እያለቁ ባከናወኑት ታላቅ ተጋድሎ ነው። ይህ ተጋድሎአቸው ህያው ሆኖ እነሆ ኢትዮጵያ ብቸኛው የጥቁር ህዝብ ተወካይ ሆና በኢየሩሳሌም ይዞታዋን አጽንታ ትገኛለች። ይህን ታሪካዊ ሃላፊነት ከምንም የማይቆጥሩ አንዳንዶች፥ ገዳማቶቻችንን ሰላም በመንሳት ብሎም ይዞታችንን አደገኛ በሆነ ሁኔታ ለሌሎች አሳልፎ በመስጠት፥የአገርንና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለማጥፋት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ ናቸው። ይህ ድርጊት ያሳሰባቸው ገዳማውያን አባቶቻችን ወደ እግዚአብሔር በማመልከት ላይ ቢሆኑም በእነርሱ ላይ ከጊዜ ወደጊዜ የሚደረገው ማስፈራራት ፥ ወከባና ድብደባ ገዳማቶቻችንን የጸሎትና የምስጋና ሥፍራ ከመሆን ይልቅ የጸብና የክርክር ቦታ እያደረገው ነው። ህጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ከተሰደደበት ጊዜ ጀምሮ ድምጹን እያሰማ ያለው እንደህ ያለው ህገ ወጥ ድርጊት በቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ስም ላይ እንዳይከናወን ነበር። አሁንም በቅዱሳት መካናት ያሉት አበው ካህናት መነኮሳት ፥ በኢየሩሳሌምና በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፥ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ቤተ እስራኤላውያን፥ እነዚህ መካናት የአብሮነት የታሪክ መነሻችን ስለሆኑ ለአንዲት ቅጽበትም ቢሆን አይናችሁን ከታሪካችሁና ከርስታችሁ እንዳታነሱ ተግታችሁ ጠብቁ ሲል ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

6. በቅርቡ በመላው ዓለም የታየውንና በተለምዶ «የኢሪያ ጉንፋን» (ስዋይን ፍሉ) በመባል የታወቀው በሽታ በመላው ዓለም ህዝብ ያሳደረውን ፍርሃት ቅዱስ ሲኖዶስ ተነጋግሮበታል። ቅዱስ ሲኖዶስ በበሽታው ለተጠቁት ፈውስን ለመላው አለም ጤንነትን እንዲሰጥ ጸሎቱን ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል፤ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም በጤና ባለሙያዎች እንደተነገረው አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ፥ ወደ እግዚአብሔርም በጸሎት እንዲያመለክቱ ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል።

7. በአሁኑ ወቅት በታየው የበሽታም ሆነ የኢኮኖሚ ቀውስ ችግሮችና ለችግሮቹ በተሰጡት መፍትሔዎች እንደምናየው ዓለም ከመቼውም በላይ እየተቀራረበ ነው። የዓለም መንግሥታት የኢኮኖሚውን ድቀት የበሽታውን ሥርጭት ለመግታት ያደረጉት የአንድነት ጥረት፥ «ግሎባሊዝም» ፍልስፍና ከመሆን አልፎ የማያመልጡት እውነታም እየሆነ እንደመጣ አመላክቶአል። ለክፉም ይሁን ለደግ ዓለም እንዲህ በሚቀራረብበት ወቅት፥ ለአገር እናስባለን የሚሉ ኢትዮጵያውያን የዛሬውን ሳይሆን የነገውን በማሰብ አንድነት ኅብረት የሚፈጠርበትን ፥ ፍትህና ሰላም የሚሠፍንበትን መንገድ ማሰብ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም በአገራችን በኢትዮጵያ ያለፍርድ የታሠሩ የፖለቲካ መሪዎች፥ የሰብአዊ መብት ተሙዋጋቾች፥ የአገር ሽማግሌዎች ከእሥራት እንዲፈቱ፥  እግዚአብሔር በአርአያውና በአምሳሉ እኛን በመፍጠሩ ለሰዎች ሁሉ የሰጠው የሰውነት መብት፥ፍትህ እንዲከበር ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል። በአንጻሩ ለሰላም ለእርቅ መቆም የአርቆ ማስተዋል ምልክት ስለሆነ በሥልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ የፖለቲካ መሪዎች ሁሉንም የህዝብ ክፍሎች ባጠቃለለ መልኩ ለእርቅና ለሰላም የሚሰባሰቡበት ሁኔታ እንዲፈጠር ቤተ ክርስቲያን ጥሪዋን ታቀርባለች።

በመጨረሻም ፳፯ኛውን ጉባኤ እጅግ በሚያስደስት ሁኔታ ላስተናገዱትና ጉባኤው ውጤታማ እንዲሆን ለደከሙት ፥ በሴይንት ፖል ሚኒሶታ ደብረ ብርሃን ቅዱስ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናት፥ የሰበካ ጉባኤ አባላትና ህዝበ ክርስቲያን እንዲሁም ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ለብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቅዱስ ሲኖዶስ  ምስጋናውን አቅርቦአል። የደብሩ ካህናትና ምእመናን የአዲስ ህንፃ ቤተ ክርስቲያን ባለቤት በመሆናቸው እንኳን ደስ ያላችሁ በማለት ደስታውን በመግለጥና ለእግዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ ጉባኤውን ፈጽሞአል።

ሴይንት ፖል ሚኒሶታ
ግንቦት ፯ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም